# የ2013 (እ.ኤ.አ) ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ነፃነት ሪፖርት

## አጭር ማጠቃለያ

ህገመንግሥቱም ሆነ ሌሎች ህግጋትና ፖሊሲዎች ለሃይማኖት ነፃነት ጥበቃ የሚያደርጉ ናቸው። በርከት ያሉ የሃይማኖቱ ተከታዮች የተሳተፉበት ሙስሊሞች ያካሄዷቸው ተደጋጋሚ ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፎች የተካሄዱ ሲሆን፤ የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ሰልፎቹን ለመበተን መጠነኛ ኃይል ተጠቅመዋል። ከዚህ አንጻር ለየት ያሉ ሁኔታዎችም ነበሩ። በነሐሴ ወር በሙስሊም ሰላማዊ ሰልፈኞችና በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች መካከል በተፈጠረ ግጭት የሦስት ሰልፈኞች ህይወት ሲያልፍ በሰባት የፖሊስ አባላት ላይ አካላዊ ጉዳት ደርሷል። በዚሁ ወር በአዲስ አበባ የኢድ አልፈጥር በዓል በተከበረበት ወቅት የፀጥታ ኃይሎች ከ1000 የሚበልጡ ሰዎችን በቁጥጥር ሥር ያዋሉ ቢሆንም፤ አብዛኞቹ ከአጭር ቆይታ በኋላ ተለቀዋል። በጥር ወር የፀጥታ ስጋት መኖሩን በመጥቀስ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፀረ ሽብር አዋጁ መነሻነት ተከሰው ጉዳያቸው በመታየት ላይ የነበረ የ29 ሙስሊሞች የክስ ሂደት ለመገናኛ ብዙሃን፥ለህዝቡና ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ዝግ እንዲሆን ወስኗል።ታህሳስ 3 ቀን ፍርድ ቤቱ የአሥሩን ተከሳሾች ክስ ሙሉ በሙሉ ሲሰርዝ አሥራ ስምንቱን የተከሰሱባቸውን ክሶች ቀንሷል። ፍርድ ቤቱ ከአልቃይዳና ከአልሸባብ ጋር ግንኙነት አላቸው ብሎ የከሰሳቸውን ሌሎች 28 ሙስሊሞች ጉዳይ በዝግ ችሎት ሲያየው ቢቆይም ከጥቅምት 19 ጀምሮ ችሎቱ ለሕዝብ ክፍት እንዲሆን ተደርጓል። ፖሊስ በአዲስ አበባ በተጠርጣሪ አሸባሪዎች ላይ መረጃ በመሰብሰብ ሰበብ በዓመቱ ውስጥ አልፎ አልፎ የአንዳንድ ሙስሊሞችን ቤት በሌሊት መፈተሹን የሚያመለክቱ ሪፖርቶች ቀርበዋል። አንዳንድ ሙስሊሞችም እንዲሁ መንግሥት በግል ሃይማኖታዊ ጉዳዮቻችን ጣልቃ ገብቷል ሲሉ በተደጋጋሚ አቤቱታ አቅርበዋል።

ሰዎች በእምነታቸው የተነሳ ማህበራዊ ጥቃት ወይም መገለል እንደደረሰባቸው የሚገልጽ ሪፖርት ቀርቧል።

የአሜሪካ አምባሳደርና የተለያዩ የኤምባሲው ባለሥልጣናት የሃይማኖት ነፃነትን በሚመለከት ከተለያዩ የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ተወያይተዋል፤ እንዲሁም ከተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በሃይማኖት ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ጋር የሃይማኖት ነፃነት ጽንሰ-ሐሳብን ለማስረጽ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። የኤምባሲው የሥራ ኃላፊዎች ከተለያዩ የሙስሊሙ ማህበረሰብ አባላት ጋር ተገናኝተው፤መንግሥት በሃይማኖት ጉዳዮች ጣልቃ ይገባል በሚል ከሚነሳው አቤቱታ ጋር የተያያዘ ውይይት አካሂደዋል።

## ክፍል 1፦ የሃይማኖቶች ስብጥር

በአሜሪካ መንግሥት ግምት መሠረት የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 93.9 (የሐምሌ 2005 ዓ.ም. ግምት) ያህል ነው። በሀገሪቱ በ1999 ዓ.ም በተደረገው የህዝብ እና ቤት ቆጠራ ከጠቅላላው ሕዝብ ወደ 44 በመቶው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ሲሆን፤ 34 በመቶው ሱኒ ሙስሊም እንዲሁም 19 በመቶው ወንጌላውያንና የጴንጤቆስጣዊ እምነት ተከታዮች ናቸው። በትግራይና በአማራ እንዲሁም በኦሮሚያ በብዛት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች የሚገኙ ሲሆን፤ በአፋር በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች በርከት ያሉ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ይኖራሉ። የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በደቡብና በጋምቤላ ክልሎች እንዲሁም በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ይገኛሉ።

ጥቂት የምሥራቅ ኦርቶዶክስ እና የሮማ ካቶሊክ፥ የይሖዋ ምስክሮች፥አይሁዳውያን፥ የኋለኛው ዘመን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት (ሞርሞኖች) እንዲሁም የባህላዊ እምነት ተከታዮች በአገሪቱ ይገኛሉ።

## ክፍል2፦ መንግሥት በሃይማኖት ነፃነት ላይ ያለው አቋም

### ሕጋዊ/የፖሊሲ ማዕቀፍ

ሕገመንግሥቱን ጨምሮ አብዛኛዎቹ ህግጋትና ፖሊሲዎች ለሃይማኖት ነፃነት ጥበቃ ያደርጋሉ። ሕገመንግሥቱ ሃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ እንደሆኑ ይደነግጋል። በሃይማኖት ላይ የተመሠረተን ስም ማጥፋትና አንድን የሃይማኖት ቡድን በሌላው ላይ ማነሳሳት ወንጀል እንደሆነ በሕግ ተደንግጓል። ይሁንና በዚህ ዓመት ይህንን የሚመለከቱ ጉዳዮች አልቀረቡም።

በአገሪቱ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠሩ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እና የሙስሊሙ ማህበረሰብ (እንዲሁም በአብዛኛው በ20ኛው ክፍለ ዘመን ወደ እስራኤል የተሰደዱ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ወይም ፈላሻዎች) በሃይማኖት ተቋምነት እንዲመዘገቡ መንግሥት አላስገደደም። ሌሎች የሃይማኖት ተቋማት ግን የባንክ ሂሳብ ለመክፈትና በፍርድ ቤት ጉዳዮች ላይ ሙሉ በሙሉ ለመሳተፍ የሚያስፈልገውን ሕጋዊ ዕውቅና ማግኘት እንዲችሉ በፍትሕ ሚኒስቴር መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል። የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጅ ከአጠቃላይ ገቢያቸው ከ10 በመቶ በላይ ከሀገር ውጭ የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ ከሆኑ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ተግባራት መሰማራት እንደማይችሉ ተደንግጓል። እነዚህም ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማራመድ፥ የብሔሮችን፥የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በሰብአዊ እና በዲሞክራሲያዊ መብቶች ዙሪያ፤በብሔሮች፥የብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን እንዲሁም ፆታዊና ሃይማኖታዊ እኩልነትን ማጠናከር፥ የህፃናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች ለማስጠበቅ፤ ግጭትን ለማስወገድና ዕርቅ ለመፍጠር ወይም የፍትሕ ሥርዓቱን ቅልጥፍና ወይም ሕግ ማስከበር አገልግሎትን የሚያከናውኑ ተግባራትን ያካትታሉ።

መንግሥት በግልም ሆነ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ሃይማኖታዊ ትምህርት እንዳይሰጥ ይከለክላል።ሆኖም ቤተክርስቲያናት የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲኖሩአቸው መስጊዶችን ቁርዓን እንዲያስተምሩ እንዲሁም በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የጋራ የሆኑ ሃይማኖታዊ እሴቶችን መሠረት ያደረጉ ክበቦች እንዲቋቋሙ ይፈቅዳል።

የመሬት ይዞታ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በመሆኑ፤ ግለሰቦች፥ የንግድ ድርጅቶችና የሃይማኖት ተቋማት መሬት ለማግኘት ለክልልና ለአካባቢ አስተዳደር ማመልከት አለባቸው።

መንግሥት ሃይማኖትን መሠረት ያደረገ የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋምን ይከለክላል።

መንግሥት ለሙስሊሞች በየሳምንቱ ዓርብ የሁለት ሰዓታት የፀሎት ጊዜ ይፈቅዳል።

**የመንግስት ተግባራት**

በነሐሴ ወር በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን የታሰሩባቸው ሦስት ኢማሞች እንዲፈቱ በሚጠይቁ ሙስሊም ሰላማዊ ሰልፈኞች እና በፖሊስ መካከል ግጭት ተከስቶ ነበር። የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ሦስት መሣሪያ የታጠቁ ሰልፈኞች መገደላቸውንና ሰባት የፖሊስ አባላት መቁሰላቸውን ዘግበዋል።

የፀጥታ ሥጋት መኖሩን በመጥቀስ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፀረ-ሽብር አዋጁ መሠረት ክስ የመሠረተባቸው የ29 ሙስሊሞች የክስ ሂደት ለመገናኛ ብዙሃን፥ ለህዝቡና ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ዝግ እንዲሆን ወስኗል። ከተከሳሾቹ መካከል መንግሥት ሃያ ስምንቱ የእስላማዊ ተቃውሞ እንቅስቃሴ አባላትና አስተባባሪዎች በመሆን ክስ ያቀረበባቸው ሲሆን አንድ ተከሳሽ ደግሞ በህገወጥ መንገድ ከውጭ አገር ኤምባሲ ገንዘብ በመቀበል ተከሷል። ታኅሣሥ 3 የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሥሩን ግለሰቦች ክስ የሰረዘ ሲሆን አሥራ ስምንቱ የተከሰሱባቸውን ክሶች ብዛት ቀንሷል። በሚያዝያ ወር ዓቃቤ ሕግ ከአልቃይዳና ከአልሸባብ ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል 28 ተጨማሪ ሙስሊሞች ላይ ክስ መስርቷል። በሐምሌ ወር ለዐቃቤ ህግ ምስክሮች የግል ደህንነት በሚል ክሱ በጊዜአዊነት በዝግ ችሎት ሲታይ ቆይቶ፤ከጥቅምት 19 ጀምሮ ግን ለሕዝብ ክፍት ሆኗል። ነሐሴ 2 ቀን፥ 2005 ዓ.ም በዋለው የኢድ አል-ፈጥር በዓል አከባበር ዕለት የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች በአዲስ አበባ ከ1000 በላይ የሚሆኑ ሰዎችን በቁጥጥር ሥር አውለዋል። በዕለቱ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ከነበሩት ሙስሊሞች መካከል አንዳንዶቹ መንግሥት ህገ መንግሥቱን እንዲያከብርና የታሠሩ ሙስሊሞችን እንዲፈታ የሚጠይቁ መፈክሮችን ይዘው ነበር። አብዛኞቹ በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሰዎች ከአጭር ቆይታ በኋላ ተለቀዋል።ፖሊስ ሐምሌ 26 ቀን ዳርሴማ ሶሪ እና ካሊድ መሐመድ የተባሉ የእስላማዊው ሬዲዮ ቢላል አርታኢዎችን በቁጥጥር ሥር አውሎ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለቋቸዋል።

ዓመቱን ሙሉ በየጊዜው የሚወጡ ዘገባዎች እንደሚጠቁሙት መንግሥት በአዲስ አበባ ከተጠርጣሪ አሸባሪዎች ጋር የተገናኘ መረጃ ለመሰብሰብ በሚል በሙስሊም መኖሪያ ቤቶች

በምሽት ድንገተኛ ፍተሻዎችን እንዳካዷል። መንግሥት ፍተሻዎቹን የሚያካሂዱ የፖሊስ አባላት የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሠረት የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይዘው ነው የሚል መልስ ሰጥቷል።

አንዳንድ የሙስሊሙ ማህበረሰብ አባላት መንግሥት በሃይማኖታቸው ውስጣዊ ጉዳዮች ጣልቃ እንደሚገባ መናገራቸውን ቀጥለዋል። ሊባኖስ በሚኖር አንድ ኢትዮጵያዊ ምሁር የመሠረተው እስላማዊ ንቅናቄን በመደገፍ ይካሄድ የነበረውን አል-አህባሽ ሥልጠና መንግሥት እንዲቋረጥ አድርጓል። የተቃውሞ ድምፅ የሚያሰሙ በርካታ ሙስሊሞች ፕሮግራሙ ባዕድ እምነትን በእምነቱ ተከታዮች ላይ ከፈቃዳቸው ውጭ ለመጫን የሚደረግና የመንግሥት እጅ ያለበት እንቅስቃሴ ነው ሲሉ መንግሥትን ወቅሰዋል።

ዋቄፋታ የተሰኘው የኦሮሞ ባህላዊ እምነት መሪዎች ህገወጥ ተብሎ ከተፈረጀው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል ጥርጣሬ መንግሥት የእምነት ቡድኑን ማገድ እንደቀጠለ ነው።

በምዝገባና በመሬት አሰጣጥ አድልዎ መፈፀሙን የሚያመለክቱ ሪፖርቶች ቀርበዋል። ከሌሎች ሃይማኖታዊ ተቋማት በተለየ፤የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በየዓመቱ እንዲመዘገቡ አይገደዱም። ሁኔታው በሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች ዘንድ እንደ አድሎአዊ አሠራር ታይቷል።

መንግሥት አንዳንድ ሃይማኖታዊ ቡድኖች ለአብያተክርስቲያናት፥ ለትምህርት ቤቶችና ሆስፒታሎች ግንባታ እንዲሁም ለመካነ መቃብር አገልግሎት የሚውል መሬት ያለክፍያ መስጠቱን ቀጥሏል።

የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ለአምልኮ ቦታዎች እና ለመካነ መቃብር የሚውሉ ቦታዎችን ሲጠይቁ በየአካባቢው የሚገኙ አስተዳዳሪዎች ጥያቄውን ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና ከእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ከሚቀርቡ ጥያቄዎች እኩል እንደማያስተናዱ በመጥቀስ ቅሬታ ያሰማሉ። በአገሪቱ የሃይማኖት ጉዳዮችን በበላይነት የመከታተል ኃላፊነት የተሰጠው የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ችግሮቹ የሚከሰቱት በአካባቢ ባለሥልጣናት የመልካም አስተዳደር ጉድለትና ለጋራ ማህበረሰባዊ አገልግሎት የሚውሉ ቦታዎች አያያዝ ዙሪያ በሚወጡ ህጎች ሳቢያ መሆኑን ገልጿል።

የብዙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጥንታዊ አብያተክርስቲያናት መሠረት በሆነችው አክሱም የሚገኙ ሙስሊሞች መስጊዶችን ለመገንባት ከአካባቢው አስተዳዳሪዎች ፈቃድ ለማግኘት መቸገራቸውን በተደጋጋሚ ቅሬታ ሲያሰሙ ቆይተዋል። በኦሮሚያ የሚገኙ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ሙስሊሞች በብዛት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት ችግር እንደሚገጥማቸው ገልፀዋል።

አንዳንድ የሃይማኖት ተቋማት በተለይም ፕሮቴስታንቶች ከ1969 እስከ 1983 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት መካከል የተወረሱባቸውን ንብረቶች በግልና ይፋዊ ባልሆኑ መንገዶች ለማስመለስ ጥረት ማድረጋቸውን ቀጥለዋል። በልማት እንቅስቃሴዎች የሚሳተፉ አንዳንድ ሃይማኖታዊ

ተቋማት የልማት ዘርፎቻቸውን በበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ እንዲያስመዘግቡና ህጋዊ መመሪያዎችን እንዲከተሉ ይጠየቃሉ፡፡

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፥ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት እንዲሁም የሲቪክ ማህበረሰብ ቡድኖች በሃይማኖት ሳቢያ የሚነሱ ግጭቶችን ለመከላከል ለሃይማኖት መሪዎች፥ ለሀገር ሽማግሌዎችና ለታዋቂ ግለሰቦች ዐውደ ጥናቶችና ሥልጠናዎችን አካሂደዋል፡፡

## ክፍል 3፡- ሕብረተሰቡ  ለሃይማኖት ነፃነት መከበር ያለው አመለካከት

ሃይማኖትና እምነትን መሠረት ያደረጉ ማህበረሰባዊ ጥቃቶችና መድሎዎች መፈጸማቸውን የሚጠቁሙ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡ በአብዛኞቹ ክልሎች በሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮችና በሙስሊሞች መካከል አንዱ የሌላውን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ከማክበር አልፎ በጋብቻ እስከመተሳሰርና እምነትን እስከ መቀየር የሚደርስ መቻቻል ይስተዋላል፡፡

በሐምሌ ወር መሃሪያ የታጠቁ ግለሰቦች በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በሚገኘው የአማራ ክልል ሼክ ኑሩ ይማም የተባሉ ኢማም ተኩሰው ገድለዋል፡፡ ፖሊስ አምስት ተጠርጣሪዎችን  በቁጥጥር ሥር አውሏል፡፡ መንግሥት በወቅቱ ድርጊቱን ‹የሃይማኖታዊ ጽንፈኞዎች› ሥራ ነው ብሎ ያውግዝ እንጂ በዓመቱ መጨረሻ ላይ በጉዳዩ ዙሪያ የተደረገ ምርመራ ውጤትም ሆነ ከግድያው በስተጀርባ ምን እንደነበረ ለማወቅ የሚያስችል መረጃ አልተገኘም፡፡

አንዳንድ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ፕሮቴስታንቶች ተከታዮቻቸውን ሃይማኖትን ለማስቀየር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በመቃወም እርስ በርስ ይወነጃጀላሉ፡፡ ይህ መወነጃጀል በሁለቱ እምነቶች መካከል ውጥረት እንዲጨምር ምክንያት ሆኗል፡፡

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትና መንግሥት ከሳውዲ ዓረቢያ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያገኝ የሚጠረጥረው የሰለፊ ቡድን በሙስሊሙ ማህበረሰብ መካከል የሚፈጥረው ተፅዕኖ እየጨመረ መምጣት እንደሚያሳሰባቸው በተደጋጋሚ ይገልጻሉ፡፡ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት እነዚህ ቡድኖች በሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል እንዲሁም በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ ውጥረት እንዲባባስ አድርገዋል ሲል ይወቅሳል፡፡

## ክፍል 4፡- የአሜሪካ መንግሥት ፖሊሲ

የአሜሪካ አምባሳደርና የኤምባሲው ተወካዮች በሃይማኖት ነፃነት ዙሪያ ከመንግሥት ጋር ውይይት አካሂደዋል፡፡ በተጨማሪም የሙስሊም ሰላማዊ ሰልፈኞችን መታሰርና አያያዝን በተመለከተ እንዲሁም በመንግሥትና በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በጋራ ስለሚሰጡ ሥልጠናዎች ተወያይተዋል፡፡

የኤምባሲው ተወካዮች በሽብርተኝነት የተከሰሱ ሙስሊሞችን የክስ ሂደት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለህዝቡ፥ ለመገናኛ ብዙሃንና ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ዝግ እስካደረገበት ቀን ድረስ ሲከታተሉ ቆይተዋል፡፡

የኤምባሲው የሥራ ኃላፊዎች ከብሔራዊና ክልላዊ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አባላት ጋር የተገናኙ ሲሆን አምባሳደሩ አዲስ ከተሾሙት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክ ጋር ተገናኝተው የአሜሪካ መንግሥት በሃይማኖት ነፃነት አስፈላጊነት ላይ ያለውን አቋም ገልፀዋል።